Eth.J. Indig. Know.Appl.Sci.
Vol.4, No.1,2026, 30-40

Ethiopian Journal of Indigenous Knowledge and Applied Sciences
Journal-homepage:https://dbujournals.edu.et ISSN 3006-7308 (online)

# የሴቶች ተሳትፎ በባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች እና ተቋማት
# ሰሜን ሸዋ፣ ኢትዮጵያ

የሴፍ ጌትነት፣ ከበደ ይመር፣ ሰርካለም ይገረሙ እና ዘቢባ መንግስቴ

Department of Amharic Language and Literature, College of Social Sciences and Humanities, Debre Birhan University, P.O. Box 445, Debre Birhan, Ethiopia

***አህጽሮተጥናት***

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሰሜን ሸዋ ዞን በተመረጡ ወረዳዎች በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትና ዘዴዎች ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ እና ሚና መመርመር ነው። የጥናቱ ዘዴ ዓይነታዊ ሲሆን የሥነተረክ እና የስነክስተት አቀራረቦችን የተከተለ ነው። ተጠኝ ወረዳዎች በኢላማ ናሙና ከተለዩ በኋላ ተሳታፊዎች በጥቆምታ የናሙና ዘዴ ተመርጠዋል። መረጃውን ለመሰብሰብ ቃለመጠይቅ፣ ቡድን ተኮር ውይይት እና መዛግብት ምርመራ ተግባራዊ ተደርገዋል። የመረጃ ትንተናውም በጽሑፍ ትንተና ስልት ተከናውኗል። የትንተናው ውጤት እንዳመለከተው በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ እና ሚና እጅግ ዝቅተኛ ነው። የሽምግልና ድርድሩን፣ ክርክሩን፣ ውሳኔውንና እርቁን የሚመሩት ወንዶች ናቸው። ሥርዓተፆታዊ አድልዎ ባህላዊ መሠረት ያለው መሆኑን ከመዛግብት ምርመራው የተገኘው የሥነቃል ትንተና ውጤት አመልክቷል። ስለሆነም ሴቶች በሽምግልና ተቋማት ከወንዶች እኩል መሳተፍ፣ የወሳኝነት ሚናቸውን መወጣት፣ ሰብአዊ፣ ማህበራዊ እና ፖሊቲካዊ መብታቸውን ማስከበር እንዲችሉ የፖሊሲ እገዛ የሚያስፈልግ መሆኑን ጥናቱ ጠቁሟል።

**ቁልፍ ቃላት፡-** ግጭት፣ ሽምግልና፣ እርቅ፣ ስርአተጾታ፣ እንስታዊነት፣ ስነተረክ፣ ስነክስተት

## 1. መግቢያ

ሰዎች በአካባቢያቸው ግጭት ሲከሰት የሕግ እና የፖሊስ ተቋማት ባልነበሩበት የጥንት ዘመን ሳይቀር መፍትሔ የሚፈልጉበት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋም እና ዘዴ ነበራቸው፤ አሁንም አላቸው። በአገራችን ኢትዮጵያም እየተሠራበት ያለ የግጭት መፍቻ ባህላዊ ስርዓት አለ።

ግጭት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል የሚነሳ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የሃይማኖት፣ የአመለካከት እና የጥቅም አለመግባባት ነው። እንደ [1] እምነት "ግጭት የማይጣጣሙ ግቦችና ድርጊቶች ባሏቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ስሜቶችን እና ፍላጎቶችን በአሸናፊነት ለመወጣት የሚደረግ ማህበራዊ ድርጊት ነው"።

የግጭት መነሻን "ይሄ ነው" ብሎ በእርግጠኝነት ለመናገር ያስቸግራል። ምክንያቱም ግጭቶች በአንድ ጊዜ በሚፈጠሩ ሁኔታዎች ብቻ የሚከሰቱ አይደሉም። የተጠራቀሙ ቅሬታዎችና ቂም በቀሎች ድምር ውጤቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ቀድም ብለው በስልጣን፣ በርእዮተዓለም፣ በሃይማኖት፣ በትዳር አለመግባባት፣ ወዘተ. ሳቢያ ቂም የተጋቡ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ምቹ አጋጣሚ ሲያገኙ ድንገት ወደ ግጭት ሊገቡ ይችላሉ። ስለዚህ ግጭት በጥቅም፣ በእምነት፣ ወዘተ. ልዩነት ምክንያት በሚፈጠር ቅሬታ ሳቢያ የሚከሰት ሲሆን አለመግባባትን መግለጫ ድርጊት ነው።

እነ [4] "የሰው ልጅ ስለግጭት የማጥናትና የመመራመር ፍላጎት ያደረበት መጽሐፍ ቅዱስ በጽሑፍ ከዋለበት ዘመን ጀምሮ ነው" ይላሉ። በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፫ እና ፬ ላይ እንደተጠቀሰው፣ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሄዋን "አታድርጉ" የተባሉትን በማድረጋቸው ሳቢያ ከፈጣሪያቸው ጋር ተጋጭተዋል። ቀጥሎም በልጆቻቸው በቃየል እና በአቤል መካከል የተፈጠረው ግጭት በቀዳሚነት ተጠቃሽ ምሳሌ ነው።

የዘመኑ ክለሳ ድርሳን እንደሚያሳየው፣ የግጭት አፈታት ዘዴ ጥናት በመጀመሪያ ከስነማህበረሰብ መስክ የፈለቀ ሲሆን ቀስ በቀስ የአለም አቀፍ ግንኙነት፣ የሕግ እና የሰላም ጥናት መስኮችም ትኩረት ስለሰጡት አድማሱን እያሰፋ መምጣት ችሏል [5]።

ግጭት ጎጂም ጠቃሚም ጎኖች ሊኖሩት ይችላሉ። ስለሆነም ግጭቶችን የምንፈታበትና የምንቆጣጠርበት ዘዴም ጎጂነቱን እና ጠቃሚነቱን ከግንዛቤ ያስገባ ሊሆን ይገባል። በግጭት አፈታት ዘዴ ላይ ጥናት ማድረግ

*Corresponding author: salamkalyimer@gmail.com.
Received: Sep 12/2025, Revised: Nov 15/2025, Accepted: Jan 17/2026, Published: Feb 1/2026.

ያስፈለገበት አንዱ ምክንያትም ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር የተቀራኘ ክስተት ስለሆነ ነው።

የግጭት አፈታት ሥርዓቶች እንደየ ማህበረሰቡ ባህል የተለያዩ እና የራሳቸው ጠንካራ እና ደካማ ጎን ያላቸው ናቸው። በመስኩ ድርሳናት ላይ ያደረግነው ንበባ እንደሚያመለክተው፣ በሰሜን ሸዋ ዞን የሚገኘው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋም እና ዘዴ ላይ የተሰራ ጥናት አንድ ብቻ ነው። እሱም ቢሆን አሁን በምን ደረጃ ላይ እንዳለ እና ምን ያህል ከዘመኑ ጋር እየተራመድ እንደሆነ የሚገልጽ ስላልሆነ በአዲስ መልክ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ስለሆነም የግጭት መፍቻ ተቋማቱን አሳታፊነት፣ የችግር አፈታት ዘዴያቸውን፣ ፍትሃዊነታቸውን ማጥናት እና ገንቢ አስተያየት ማቅረብ የማህበረሰቡ ሰላም እና ደህንነት ቀጣይነት እንዲኖረው ያግዛል። ከዚህም ባለፈ፣ ይህ ጥናት ለፖሊሲ አውጭዎች፣ ለባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት፣ ለትምህርት ባለሙያዎች እና ለጥናት አድራጊዎች የመረጃ ምንጭ በመሆን እንደሚያገለግል ይታመናል። በዚህ መነሻነትም ጥናቱ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል።

(1) በሰሜን ሸዋ ዞን ማኅበረሰብ ዘንድ ለግጭት መንስኤ የሆኑት ዋና ዋና ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? (2) በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ የሴቶች ተሳትፎ እና ሚና ምን ይመስላል? እና (3) ባህላዊ የግጭት መፍቻ ብልሃቶቹ ምን ምን ደካማ እና ጠንካራ ጎኖች አሏቸው? የሚሉት ናቸው።

## 2. የጥናቱ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትና ዘዴዎች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ እና ሚና ምን ድርሻ እንዳለው መመርመር ነው። ስለሆነም ይህን ዓላማውን ከግብ ለማድረስ፣ ጥናቱ የዓይነታዊ ዘዴ አካል የሆኑትን ስነክስተታዊ[1] እና ትረካዊ አቀራረብ ስልቶችን ተከትሏል። ምክንያቱም ትረካዊ የአቀራረብ ስልት በባህላዊ የሽምግልና ሥርዓት የሚከናወነውን የግጭት አፈታት ክስተት በግለሰብ ደረጃ የሚናገሩትን በጥልቅ እና በስፋት ለመረዳት ስለሚያስችል ነው [6]። ስነክስተታዊ አቀራረብ ስልት ደግሞ ግለሰቦች ስለግጭት አፈታት ከገጠማቸው ተመሳሳይ ክስተት መካከል እጅግ ተፈላጊውን[2] መረጃ መርጦ በማቀናጀት ለመተንተን ስለሚያስችል ነው [7]።

### 2.1 ንድፈሐሳባዊ ማሕቀፍ

ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች ያሉባት አገር ናት። እነዚህ ብሄረሰቦች ከጥንት ጀምሮ በመካከላቸው የሚከሰቱ ግጭቶችን በራሳቸው ባህላዊ መንገድ ሲፈቱ ኖረዋል። ይሁን እንጂ የግጭት መፍቻ ዘዴዎቹ በጥልቀት አልተጠኑም። ስለሆነም የግጭቶቹን የአፈታት ዘዴ፣ ዓይነት እና የተሳታፊዎቹን ማንነት እና ሚና በአግባቡ መተንተን እና መረዳት የሚያስችሉ ንድፈሐሳባዊ ማሕቀፎችን ለማግኘት አባዊ ስርዓትን፣ እንስታዊነትን እና ባህላዊ የግጭት መፍጫ ብልሃቶችን በተመለከተ ቀደምት ድርሳናትን መከለስ አስፈልጓል።

አንዱ ማሕቀፍ አባዊ ስርዓት ሲሆን የወንዶችን የበላይነት የሚያመለክት ነው። አባዊ የሚለው ፅንሰሐሳብ የቤተሰብ ዝምድናን፣ ሥልጣንን እና ማህበራዊ የበላይነትን ያመለክታል [9]። ይህ ማህበራዊ የበላየነት በተፈጥሮ የተገኘ ሳይሆን ማህበራዊ ሥሪት ነው። ስለሆነም በሥሩ ያለውን ሀብት፣ ሥልጣን እና መብት በቁጥጥሩ ሥራ ያደርጋል፤ ጠቅልሎ በበላይነት ያስተዳድራል። በዚህ ምክንያት  አባዊ ስርዓቱ የሴቶችን የማስተዳደር፣ የሀብት እና የሥልጣን ክፍፍል እኩልነት፣ የውሰኔ ሰጭነት ድርሻ ሳይቀር ይነጥቃል።

የመስኩ ተመራማሪዎች እንደሚያስረዱት፣ ሥነቃል እና የሃይማኖት መጻሕፍት ስርዓተፆታን ጉዳያቸው ቢያደርጉም የሴቶችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ሚና ከወንዶች ጋር እኩል አድርገው አያቀርቡም። ስለሆነም አስተምህሯቸው ፆታዊ አድልዎ ይንጸባረቅበታል። ለአብነትም በኡጋንዳ ሥነቃል ላይ የተደረገው ጥናት እንደዘገበው፣ የሥነቃሎቹ ጭብጥ ሲተነተን አባዊ ስርዓትን የሚያጠናክር ነው [10]።

ሌላው ማሕቀፍ እንስታዊነት ነው። ሴት እና ወንድ በተፈጥሮ እኩል ቢሆኑም፣ የስርዓተፆታ አወቃቀር እና ግንኙነት እንደሚያመለክተው የወንዶች የበላይነት ገዝፎ ይስተዋላል። ይህን የእኩልነት ተባልጦ መነሻ በማድረግ የእንስታዊነት እርእዮተዓለም የአባዊውን ስርዓት በመቃወም በ1960ዎቹ ሊከሰት ችሏል። የተለያዩ የእንስታዊነት ንድፈሐሳቦች ቢኖርም የዚህ ጥናት ትኩረት "ሌበራል" እንስታዊነት የሚለው ነው።

እንስታዊነት ሴቶች በኢኮኖሚ፣ በባህል፣ በፖለቲካ እና በማህበራዊ ተሳትፎ ከወንዶች እኩል ድርሻ እና ሚና እንዲኖራቸው ለመታገል እና ለማስተካከል የሚያስችሉ ስልቶች እያቀረበ ያለ ንድፈሐሳብ ነው። ስለሆነም ይህ ማሕቀፍ ለዚህ ጥናት መሠረት ነው።

ሦስተኛ ንድፈሐሳባዊ ማሕቀፍ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ብልሃቶችን የሚመለከት ነው። በኢትዮጵያ ባህላዊ የግጭት አፈታት ብልሃቶችን በተመለከተ የተሠሩት ጥናቶች እጅግ ወስን [11; 21; 13] ናቸው።

በ1960 ዓ.ም የተጻፈ ዘገባ እንደሚያስረዳው፣ በሰሜን ሸዋ ዞን የተጉለት እና ቡልጋ አካባቢ ነዋሪዎች፣ የአገር ሽማግላዎችን መርጠው የተጣላውን በማስታረቅ እና የተበደለውን በማስካስ ግጭቶችን ይፈታሉ። ግጭቱ ግድያ የተፈጸመበት ከሆነ ደጎሞ የሟች ወገኖች "ከዚህ እስከ እዚህ ድረስ ባለው የእርስታችን ቦታ እንዳይደርስብን" ብለው ባመለከቱት መሠረት ገዳዩ ከተከለለው ቦታ እንዳያልፍ ይገዘታል። ከዚያም  ወደ ግጭት በድጋሚ እንዳይገቡ ባለደሙን እና ገዳዩን

የሸንጥ ሥጋ ያቀራርጧቸዋል። በዚህ መንገድ ግጭቱ ይፈታል፤ እርቅ ይወርዳል [11]።

በሽምግልና የሚደረግ እርቅ ጊዜን፣ ጉልበትን እና ገንዘብን በመቆጠብ ረገድም በፍርድ ቤት ከሚደረገው ሙግት የበለጠ ተመራጭነት አለው። በሰሜን ጎንደር ዞን ያሉ ነዋሪዎች ማህበራዊ ተሰሚነት፣ የመናገር ችሎታ፣ የኢኮኖሚ አቅም ያለውን አባዋራ ለሽምግልና ይመርጣሉ። የተጣሉት ሲታረቁም የጠላ እና የቀሎ ግብዣ ያደርጋሉ [14]።

በቤተሰብ መካከል ለሚነሱ ግጭቶች የኢኮኖሚ ጉዳዮች፣ የባህሪ ችግር እና ቅናት በመንስኤነት ተጠቃሽ ናቸው። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በባል እና ሚስት መካከል ለሚነሣ ግጭት በወሲብ ጊዜ የሚፈጠር አለመጣጣም አንዱ ምክንያት ነው። እነዚህን ግጭቶች ለመፍታት በሽማግሌ እርቅ ማድረግ፣ በቤተሰብ መካከል ውይይት መክፈት፣ አጉል ግንኙነትን ማቋረጥ እና ፍቺ መፈጸም የመፍትሔ መፈለጊያ ብልሃቶች ሆነው ተተግብረዋል [13]።

## 2.2 የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱ ንድፍ እንደሚከተለው በሥዕላዊ መግለጫ 1 ቀርቧል።




ሥዕል1፡- ለዚህ ጥናት እንዲያመች ከ[17] ተሻሽሎ የተወሰደ ንድፍ

ከዚህ በላይ በሥዕላዊ መግለጫው እንደቀረበው፣ ናሙና መረጣው፣ መረጃ ስብሰባው፣ መረጃ ስነዳው፣ መረጃ መረጣው እና መረጃ ትንተናው የትረካዊ እና የስነክስታታዊ አቀራረቦችን በመከተል ተከናውነዋል። ምክንያቱም የታወቀ ንድፈሐሳባዊ ማሕቀፍን ተከትሎ በተዋቀረ መንገድ የጥናቱን ንድፍ ማቀድ በቅደም ተከተል የሚከናወነውን ክስተት በቅጡ ለመረዳት ያስችላል [17]።

## 2.3 የጥናቱ ቦታ

ይህ ጥናት የተካሄደው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ በሰሜን ሸዋ ዞን ነው። ዞኑ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን 9°0ˈ 0 ʺ - 10°0ˈ 0ʺ ላቲቲዩድ መካከል በሰሜን እና በምሥራቅ 039° 0ˈ 0ʺ- 040°00ˈ 0ʺ ሎግቲዩድ መካከል ይገኛል።




ሥዕል2. የዞኑ መልካ ምድራዊ አቀማመጥ

ዞኑ ካለው የባህል ሀብት አንጻር ይህን ጥናት ለማድረግ ተስማሚ ሆኖ በመገኘቱ የተመራማሪዎችን ትኩረት መሳብ እና የጥናቱ ተተኳሪ መሆን ችሏል።

## 2.4 ናሙና አመራረጥ

በተጠኝነት በተመረጠው የሰሜን ሸዋ ዞን 24 ወረዳዎች ይገኛሉ። ከእነዚህ ወረዳዎች መካከል 9 ወረዳዎች በኢላማ ናሙና ተመርጠው የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል። እነሱም ደብረብርሃን፣ ሞረትና ጅሩ፣ ሸዋ ሮቢት፤ ምንጃር፣ መርሐ ቤቴ፣ ሚዳ ወረሞ፣ አንጎለላና ጠራ፣ መሀል ሜዳ እና ኤፍራታና ግድም ናቸው።

## 2.5 መረጃ አሰባሰብ

በመረጃ ስብሰባ ቅድመዘግጅት ወቅት በመስክ ሊሰሩ የሚችሉ ተግባራትን በተመለከተ የተግባር እና የጊዜ ዕቅድ በዝርዝር ተዘጋጅቷል።

ለጥናቱ ወደተመረጡ አካባቢዎች ከመኬዱ በፊት በርእሰጉዳዩ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችና መጻሕፍት ተከልሰው ተገቢው መረጃ ተወስዷል። ምክንያቱም በባህል ጥናት አከዋወን ዘዴ መሠረት "ተመራማሪው ጥናቱን መጀመር ያለበት በቤተመጻሕፍት እና በመዛግብት ክምችት ክፍል በመገኘት ነው" [15]።

የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ሦስት ሲሆኑ እነሱም ቃለመጠይቅ፣ ቡድን ተኮር ውይይት እና መዛግብት ምርመራ ናቸው።

የጥናቱ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለመጠይቅ ነው። ቃለመጠይቁ በከፊል የተዋቀረ ሲሆን ከጥናቱ ዓላማዎች አንጻር ተገቢውን መረጃ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ ተሰናድቷል። ቃለመጠይቁ፣ ግለሰቦች በባህላዊ የግጭት አፈታት ተቋም፣ ዘዴው እና ተሳታፊዎቹ ላይ ያላቸውን ልምድ እና ያጋጠማቸውን

ክስተት በትረካ መልክ እንዲናገሩ በማድረግ ላይ ያተኮረ ነው። የቃለመጠይቁ አከዋወን ሂደትም እንደሚከተለው በሥዕል 1 በቀረበው ንድፍ ተካሂዷል።




ሥዕል 3፡- የቃለመጠይቅ አከዋወን ሂደት ከ[6] ንድፍ ተሻሽሎ የተወሰደ

በመጀመሪያ ቃለመጠየቁን በድምፅ መቅረጫ መቅዳት፣ ከዚያም ወደ ምዝግብ መረጃነት መቀየር፣ ቀጥሎም ኮድ በመስጠት በጭብጥ መለየት፣ በመጨረሻም በቅደም ተከተል ማደራጀትና ለትንተና ዝግጁ ተደርጓል።

ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቡድን ተኮር ውይይት ነው። የተወያይ ቡድኑ አመራረጥም በእርእሰጉዳዩ ላይ የተለያየ አመለካከት ይኖራቸዋል ተብለው የሚገመቱ አባላትን ያካተተ ሲሆን ከሴት አራት ከወንድ ሦስት በድምሩ ሰባት አባላትን ይዟል። ቡድን ተኮር ውይይቱ በሽምግልና አመራረጥ ሂደቱ እና በግጭት መነሻ መንስኤዎቹ ላይ ያተኮረ ነበር። ምክንያቱም ይህ ዘዴ ሁለቱንም ወገኖች ያማከለ እና በጉዳዩ ላይ በውይይት የዳበረ መረጃ ለማግኘት ስለሚያስችል ነው።

የቃለመጠይቁ እና የቡድን ተኮር ውይይቱ በድምፅ እና በምስል መቅረጫ መሣሪያ አማካኝነት ተቀርጸው መረጃዎቹ በአግባቡ ተሰንደዋል።

ሦስተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የመዛግብት ምርመራ ነው። በወረዳ እና በዞን የመዛግብት ክምችት ክፍል በመገኘት ሥነቃሎች ተሰብስበዋል። በተለይም የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ ዬያስችሉ የቃል ግጥሞች እና ምሳሌያዊ አነጋገሮች በመረጃነት ተወስደዋል።

## 2.6 **የመረጃ መተንተኛ ዘዴ**

እያንዳንዱን የምርምሩን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ እንዲቻል ተፈላጊውን መረጃ ከቃለመጠይቅ፣ ከቡድን ተኮር ውይይት እና ከመዛግብት ምርመራው በመምረጥ በሦስት ጎንዮሻዊ የድግግፎሽ ስልት ትንተና ተደርጓል።

በቅድሚያ በትረካዊ የመረጃ አተናተን ስልት መሠረት፣ መጀመሪያ ከእያንዳንዱ መረጃ አቀባይ በትረካ የተገኘውን ታሪክ በጭብጥ በመከፋፈል እና በቅደም ተከተል በማደራጀት ከተተነተነ በኋላ እንደገና በስነክስተታዊ አራረብ ስልት መሠረት ከእየ ግለሰቦቹ የተገኘውን ፍሬ ነገር በማቀናጀት እጅግ ተፈላጊውን (essence) መልእክት ለማግኘት በሚያስችል መልኩ ተዋቅሯል።

ከዚያም ከቡድን ተኮር ውይይት ከተገኘው መረጃ ጋር በማቀናጀት ትንታኔው ቀርቧል። ከመዛግብት ምርመራው የተገኙት ምሳሌያዊ አነጋገሮችም እንዳስፈላጊነቱ ደጋፊ እየሆኑ ገብተዋል።

## 3. **የጥናቱ መረጃ ትንተና**

ትንታኔው የተደረገው በጥናቱ መሠረታዊ የምርምር ጥያቄዎች መሪነት ነው። ስለሆነም እያንዳንዱን ጥያቄ ለመመለስ እንዲቻል ከቃለመጠይቅ፣ ከቡድን ተኮር ውይይት እና ከመዛግብት ምርመራው ተገቢው መረጃ እየቀረበ ትንተናው ተከናውኗል።

**የምርምር ጥያቄ** 1. በሰሜን ሸዋ ማህበረሰብ ዘንድ ለግጭት መነሻ መንስኤ የሆኑት ዋና ዋና ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

በእነዋሪ ቀበሌ 01 ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ እታበዝ ብዙአየሁ እንደሚሉት፣ በየአመቱ ጎጆ የሚወጡት ወጣቶች ለቤት መሥሪያ እና ለእርሻ የሚሆን መሬት ይፈልጋሉ። ትምህርታቸውን ጨርሰው የተቀመጡት ወጣቶችም የመነገጃ ወረት እና ቦታ ይሰጠን ይላሉ። ለልጆቹ መሬት ተከፍሎ እና ከብት ተሸጦ ገንዘብ እንዲሰጥ እናት ስትፈቅድ አባት ለምን ይላል? በዚህ የተነሣ በእናትና በአባት መካከል ግጭት ይፈጠራል።

የእርሻ መሬት ድንበር ገፋህብኝ በማለት የሚጣሉ አሉ። መረጃ አቀባያችን እንደተናገሩት፣ በ1989 ዓ.ም. በተካሄደው የእርሻ መሬት ድልድል ፍትሃዊ አልነበረም። የአንዱ ድርሻ ሰፊ የሌላው ጠባብ ነበር። ጠባብ የመሬት ድርሻ ያለው የሌላውን ድንበር በመግፋት እርሻውን ለማስፋት ይጥራል። ድንበሩ የተገፋበት ደግሞ ለምን? በማለት ይገጥማል። ይህም ሌላው የግጭት መነሻ ምክንያት ሆኖ ይቆጠራል።

አርሶ አደሩ ያለውን መሬት ለእርሻ ተግባር ስለሚያውል ለግጦሽ የሚሆን ቦታ አይተርፈውም። እርግጥ ነው በየቀበሌው የግጦሽ መሬት ተብሎ ሁሉም ሰው በጋራ ከብቶቹን የሚያሰማራበት የተወሰነ ቦታ አለ። ነገር ግን ከከብቶቹ ብዛት አንጻር ሲታይ ቦታው በጣም አነስተኛ ነው። ስለሆነም ከብቶቹ የሚበላ ለማግኘት ሲሉ ወደ ሌላ ሰው አዝመራ ይገባሉ። በዚህን ጊዜ አዝመራው የተበላበት ከብቶቹን ይደበድባል ወይም በማገት ካሣ ይጠይቃል። በዚህ አጋጣሚ ከከብቱ ባለቤት ጋር ጠብ ይፈጠራል።

ሌላው መረጃ አቀባያችን ጉዳዩን ሲያስረዱ፣ አንዳንድ አካባቢ በመስኖ ውሃ አጠቃቀም ሳቢያ ጠብ ይፈጠራል። ገበሬዎች የመስኖ ውሃ የሚጠቀሙት በተራ ገብተው ነው። ይሁን እንጂ ተራው ባልሆነ ቀን የውሃውን ቦይ ወደ ራሱ የእርሻ ማሳ የሚያዞር ሰው ያጋጥማል።

በዚህን ጊዜ ባለተራው “እንዴት ያለ ተራህ ልጠቀም ትላለህ?” በሚል አተካራ ውስጥ ይገባል።

ሌላው የግጭት ዓይነት በባል እና በሚስት መካከል የሚከሰተው ነው። በባል እና በሚስት መካከል የሚከሰተው ግጭት የተለያዩ ምክንያቶች አሉት። አንዱ ቅናት ነው። በቅናት ምክንያት ባል እና ሚስት ከከፋ የግጭት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። ከትረካው የተገኘውን መረጃ እንመልከት።

*በድሮ ጊዜ በፍቅር የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ። ሚስትዮዋ ባልዋ ወደ እርሻ ሲሄድ እሷ በድብቅ ከውሽማዋ ጋር ትቀብጥ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ባል አውድማ ጥሎ ስለነበር እዚያው ነው የሚያድረው ብላ ውሽማዋን ቀጠረችው። ባልየው ካለወትሮው አምሽቶ እራቱን እየበላ ሳለ ውሽምየው ደግሞ በቀጠሮው ሰዓት መምጣቱን ለመግለጽ የባጡን እንጨት ነካ ነካ አደረገው። ሴትዮዋም ደንግጣ የምታደርገው በጨነቃት ጊዜ አንድ መላ መጣላት። ይሄውም ቀን ስትፈጭ ወደ ነበረው ወፍጮ ሄዳ የምትፈጭ በመምሰል በዘፈን*

*‘ተው በሬ ተው በሬ ባጡን አታፍርሰው*

*እራቱን ይበላል ቅራት የሚሄድ ሰው’*

*በማለት ባልዋ እቤት መኖሩን በዘዴ ነገረችው። ባልዮውም ምስጢሩ ገባውና፣*

*‘እኛ የማናውቀው ሰዋሰው ጨዋታ*

*ቀን ካልተቀጠረ በሬ አይመጣም ማታ’*

*በማለት በጥይት ገደላት ይባላል።*

(መረጃ አቀባይ፡- አቶ ደረጀ አዝዛቸው)

መረጃ አቀባያችን እንደተረኩልን ይህ ተረት ባል ሚስቴ በትዳሬ ላይ ወስልታለች በሚል ቅናት ተነሳስቶ ባልተረጋገጠ መረጃ እንዴት በሚስቱ ላይ ግድያ እንደፈጸመ ያሳያል። ስለዚህ ተረቱ ለትዳር መፍረስ አንዱ ምክንያት ቅናት መሆኑን ያሳያል።

ተረቱ በአቀራረቡም ሆነ በይዘቱ የአባዊውን ስርአት ለማጎላት የተሰናዳ ይመስላል። ምክንያቱም ሴቷን ብቻ ሴሰኛና ወንጀለኛ ያደረገ እና ፍትሀዊነት የጎደለው ነው።

በመረጃ ትንታኔው ከግጭት መነሻዎች አንዱ ተደርጎ የተቀጠረው ስካር ነው። ስካር ለድንንገተኛ ግጭት አንዱ መንስኤ ነው። መረጃ አቀባዮቻችን እንደተረኩልን በገበያ ቀን፣ በዓመት በዓል፣ በሰርግ፣ በማህበር፣ ወዘተ. ጊዜ እየተጠጣ ቀረርቶና ፉከራ ይጀመራል። አንድ ሰው ሞቅ ብሎት በሚያቅራራበት ጊዜ ግጥሞቹ ሌሎችን የሚያስቀይሙ ከሆነ ወደ ግጭት ይገባል። ቀጥሎ የቀረቡት የቀረርቶና የፉከራ ቃል ግጥሞችን እንመልከት።

ረጅም ሚኒሽር ተኩሱም ረጅም ነው፤

ከተጣሉ ወዲያ እርቁ ለምንድን ነው?

በዚህ ቃል ግጥም እንደተነገረው፣ ሰዎች በተለያየ ምክንያት ይጣላሉ። አንዳንዱ ግጭት በአንደኛው ወገን ላይ የከፋ ግፍና መከራ ያደርሳል። በዚህ ጊዜ እርቁን ለመግፋት ሲል ለአስታራቂዎቹ ቅሬታውን ወይም እምቢታውን በዚህ መልኩ ይገልፃል። ይህን ሁኔታ በይበልጥ የሚያጠናክርልን የሚከተለው የፉከራ ግጥም ነው።

አሳር ነው አለ አሳር መከራ

በሰው አዳራሽ ገብቶ ፉከራ

አሽሟጣጭ ቆሞ በቀኝ በግራ።

ይህ ግጥም የሚያሳየን አሽሟጣጭ ወይም ተቺው ቢኖርም መፎከር እንደሚያስፈልግ ነው። በዚህ ፉከራ አማካኝነት መልዕክት የሚደርሳቸው እና ስሜት ውስጥ የሚገቡ ታዳሚዎች ይኖራሉ። በዚህም አፍ እላፊ መነጋገር ስለሚኖር ወደ ግጭት ይገባል።

በአብዛኞቹ መረጃ አቀባዮቻችን እምነት በግለሰቦች መካከል ለሚፈጠሩት ግጭቶች ዋና ዋናዎቹ መንስኤዎች የእርሻ መሬት፣ የግጦሽ ቦታ፣ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም፣ ስካር፣ ቅናት እና ውርስ ናቸው።

**የምርምር ጥያቄ** (2) በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ የሴቶች ተሳትፎ ምን ይመስላል?

ከባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት አንዱ ሽምግልና[3] ነው። የተጣሉና የተኳረፉ፣ የተቀያየሙና የተበቃቀሉ ሰዎችን ወደ ፍርድ ቤት ሳይሄዱ፣ ሳይወጡና ሳይወርዱ በመንደራቸውና በጎጣቸው ያሉ ሰዎችን መርጠው ሽማግሌ በማድረግ "ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ" እንደሚባለው “አንተም ተው! አንተም ተው!” ብለው መክረው፣ ተቆጥተው የሚያስማሙበት ሀገራዊ ልማድ ነው።

ከመረጃ አቀባዮቻችን አብዛኞቹ እንደሚሉት፣ በሰሜን ሸዋ ዞን የሚከናወነው የሽምግልና ስርዓት ሴቶችን በሽምጋይነት አያካትትም።

ሥነቃሉም ቢሆን ስለሴቶች ወኔ እና ጀግነት አሉታዊ መልክት ያስተላልፋል። ለአብነትም የሚከተለውን እንመልከት።

“ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንደ አባቱ

ስጡት አመልማሎ ይፍተል እንደ እናቱ”

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ቃል ግጥም፣ ጀግንነትና ጉብዝና ለወንድ ሲሰጡ በአንጻሩ ፍርሀት፣ ሽንፈትና እቤት መዋል ለሴት እንደተተዉ ማሳያ ነው። የቃል ግጥሙ ሴቶች ከወንዶች ያነሱ መሆናቸውን አምነው እንዲቀበሉ እና በልቦናቸው እንዲያሰርፁ የተዛባ መልዕክት ያስተላልፋል።

በዚህ የተነሣም ሴቶች ለሽምግልና የሚበቃ አቅም እና ወኔ የላቸውም የሚል እምነት በህብረተሰቡ ስነልቦና ተፀንሶ እንዲጎለብት አድርጓል።

ስለሆነም የሽምግልና አባላቱ ወንዶች ናቸው። በዚህ ሳቢያም የባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋሙም አባዊ ነው። የመረጃ ትንተናው እንደሚያመለክተው፣ በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ ውስጥ የሴቶች ሚና እጅግ ዝቅተኛ ነው። ድርድሩን፣ ክርክሩን፣ ውሳኔውንና እርቁን በዋናነት የሚመሩት ሽማግሌዎች ወንዶች ናቸው።
በወንዶች የበላይነትና ጠቅላይነት የሚመራው ይህ ተቋም ሴቶች የማይሳተፉበትን አሳማኝ ያልሆነ ምክንያት ያቀርባል።

**የምርምር ጥያቄ** (3) ባህላዊ የግጭት መፍቻ ብልሃቶቹ ምን ምን ደካማ እና ጠንካራ ጎኖች አሏቸው? የሚሉት ናቸው።

ሽምንግልና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን በመፍታት ረገድ እጅግ አስፈላጊ ከሚባሉት ባህላዊ ተቋማት አንዱ ነው። ይህን አስፈላጊነቱን ማህበረሰቡ ጠንቅቆ ያውቃል፤ ይህንም በስነቃሉ ሳይቀር ለተተኪው ትውልድ እንደሚከተለው ያስተላልፋል።

“ሁለት ጥቁር በሮች አባይ ዳር ገጥመው

ሁሉም ገደል ገቡ ገላጋይ አጥተው።”

በማህበረሰቡ አመለካከት አርሶ አደሩ ብርቱ ነገር ሲገጥመው፣ በሬን በተምሳሌትነት ይጠቀምበታል። በሬ የጎልማሳነት፣ የአባወራነት ከዚህ አልፎ የጀግንነት ወካይ ነው። በሬ ለአርሶ አደሩ እጅግ አስፈላጊና የህልውናው መሰረት ነው። ስለሆነም በሬን ያህል ክቡር ጥሪት በገላጋይ እጦት ገደል መግባቱን ይገልጻል።

ይህ ተምሳሌታዊ የቃል ግጥም የተጣሉ ሰዎች ተያይዘው እንዳይጠፉ መገላገል አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳል። በዚህ ረገድ ሽምግልና በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ከፍተኛ ሚና ያመለክታል።

የመረጃ ትንታኔያችን እንደሚያመለክተው፣ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋሙ ሦስት ድክመቶች ይስተዋሉበታል። ከእነዚህም አንዱ ሴቶችን በሽምግና አለማሳተፍ ነው።

በቡድን ተኮር ውይይቱ እንደተስተዋለው፣ በአካባቢው ልማድ መሠረት፣ ሽማግሌዎች በባለጉዳዮች የጋራ ስምምነት ይመረጣሉ። ባለጉዳዮችም ተስማምተው በመረጧቸው ሽማግሌዎች የሚሰጣቸውን ዳኝነት የመቀበል የውዴታ ግዴታ አለባቸው። የስነቃል ባህሉም ይህን ያበረታታል። ቀጥሎ የቀረበውን ምሳሌያዊ አነጋገር ለአብነት እንመልከት።

“በቀረጡት በትር ቢመቱ
በመረጡት ዳኛ ቢረቱ”

ከዚህ በላይ የቀረበው ምሳሌያዊ አነጋገር እንደሚያስረዳው፣ ሽማግሌዎች ጉዳዩን በጥሞና ከመረመሩ፣ የዓይን ምስክሮችን ካዳመጡ፣ መረጃውን በማስረጃ ካረጋገጡ በኋላ መፍትሄ ይሆናል ያሉትን ፍርድ ይወስናሉ። ውሳኔው ሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች እኩል እንደማያስደስት ይገመታል። በተለይም የተረታው ወይም የተፈረደበት ወገን ውሳኔውን የመቀበል የውዴታ ግዴታ አለበት። ምክንያቱም ይዳኙኛል ብሎ ለመረጣቸው ሽማግሌዎች ፍርድ ተገዥ መሆን ይጠበቅበታል። ስነቃሉ፣ ባለጉዳዮች በመረጡት ሽማግሌ ጥፋተኛነት ቢፈረድባቸው እንኳ መቀበል እንዳለባቸው ያስተምራል።

ነገር ግን ሽማግሌዎቹ በስምምነት የሚመረጡ ቢሆንም ሴት ባለጉዳዮች የራሳቸውን ሴት ሽማግሌ እንዲመርጡ ዕድል አይሰጥም። ለዚህም አድልዎ የሚከተለውን ምሳሌያዊ አነጋገር እናጢነው።

“የመቀናጆ በሬ ወደ አገሩ ይሰባል”

የመቀናጆ በሬዎቹ ከተለያየ ሰውና ከተለያየ ሰፈር የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ። እርስ በርስ መናበብ ሲያቅታቸው ወደ የመጡበት አቅጣጫ በማድላት ይስባሉ። ይህም ሥራውን የተቃና እንዳይሆን ያደርገዋል።

የምሳሌያዊ ንግግሩ ትኩረትም በተለይ ባል እና ሚስት ተጣልተው ጉዳያቸው በሽምግና እንዲያልቅ ሲስማሙ የሚመርጧቸው ሽማግሌዎች ወንዶች ብቻ ከሆኑ የሴቷን ውስጣዊ በደል ለመረዳት ባህሉ ይጋርዳቸዋል። ለባልየው ስለሚያግዙ ሚስትየዋን ይበድሏታል።

ሌላው ድክመት አይነኬ ጉዳዮች በሽምግልና ላይ በይፋ እንዳይቀርቡ መገደባቸው ነው። ሚስቶች ከባሎቻቸው ጋር ከማይግባቡባቸው እና ወደ ፍቺ ከሚደርሱባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት አለመጣጣም እንደሆነ ከቃለመጠይቅ የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ያመለክታል።

መረጃ አቀባዮቻችን ደጋግመው እንደነገሩን፣ በባል እና ሚስት መካከል ያለ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ችግር በይፋ ለሽምግልና የማይቀርብ አይነኬ በደል ነው። ቀጣዩን መረጃ ከቃለመጠይቁ ለአብነትም እንመልከት።

**ተመራማሪ፡-** የባለትዳሮች የግጭት ምክንያት ከሽሮ እና ከበርበሬ ባለፈ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ጊዜ አለመጣጣም ሊሆን ይችላል?

**መረጃ አቀባይ፡-** አዎ፤ ምን ይጠፋል እሱማ

**ተመራማሪ፡-** እንዴት ይገልጹታል?

**መረጃ አቀባይ፡-** እሃሃ ቂቂቂ እምህ ወንዶቹ ዝም ብለው ቢተኙ እንኳ ጥሩ ነበር። ግን …

**ተመራማሪ፡-** እናስ?

**መረጃ አቀባይ፡-** ሴቷን ይጿጨራሉ፤ ይወራጫሉ፤ እንቅልፍ እንቢ ይላቸዋል፤ ኸረ ምኑ ቅጡ! …

ይህን ጉዳይ ሚስቶች በሽምግልና ዓውድ በይፋ ለወንድ ሽማግሌዎች ለማቅረብ ባህሉም አይፈቅድም። በደሉ ሳይታወቅ እና ዘላቂ መፍትሄ ሳይፈለግለት እንደተሸፋፈነ በሽማግሌ ግፊት "ታረቁ" ይባላል። በጫና እንዲታረቁ ይደረጋል። ይሁን እንጂ ውሎ አድሮ ችግሩ አመርቅዞ እንደገና ያገረሻል። ጉዳዩ አይነኬ መሆኑ ሴቶች በራሳቸው ጉዳይ ላይ ወሳኝ እንዳይሆኑ አሉታዊ ተጽእኖ አድርጓል። ምናልባትም ሴቶች በሽምግልና ምርጫው ተሳታፊ አባል ቢሆኑ ይህን ጉዳዩ ማቀረብ ከባድ ላይሆን ይችላል።

ሦስተኛው የቆየ የባህል ተጽእኖ መኖሩ ነው። የቃለመጠይቅ መረጃው እንደሚያሳየው፣ በምክንያት ለሚያምን ሰው ተቀባይነት ባይኖረውም፣ ባባህሉ ውስጥ "ሴቶች ለሽምግልና ብቁ አይደሉም፤ በአደባባይ የመሳተፍ ልምድ የላቸውም" የሚል አሉታዊ አመለካከት በስነቃሉ አማካኝነት ተሰራፍቶ ይገኛል።

"የሴት ዳኛ የነብር እረኛ የለውም"

ከዚህ በላይ የቀረበው ምሳሌያዊ አነጋገር ከሴቶች ተፈጥሯዊ ማንነት ጋር የማይሄድ ጊዜው ያለፈበት መልዕክት ያለው ነው። ምክንያቱም በዚህ ዘመን ሴቶች ዳኛ ሆነው ችሎት ሲያስችሉ፣ ፍርድ ሲሰጡ ማየት የአደባባይ ምስጢር ነው። ስለዚህ "የሴት ዳኛ የለም" ብሎ ማስተማር ተጨባጭ እውነታን መካድ ነው።

"የሴት መብቷ በማጀቷ"

ይኸኛው ምሳሌያዊ አነጋገርም ቢሆን ሴት ከማጀት ውጭ መብት እንደሌላት የሚያትት ነው። ሆኖም ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ለሚለው ጥያቄ ተገቢ ምላሽ አይሰጥም። ስለዚህ መታረም ያለበት አመለካከት እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም።

"ወንድ ባለ በዕለት ሴት ባለች በዓመት ይፈጸማል"

ከዚህ በላይ የቀረበው ምሳሌያዊ አነጋገር የሴት ትዕዛዝ ቶሎ ተፈፃሚነት እንደሌለው የሚናገር ነው። ነገር ግን አንድ ትዕዛዝ ቶሎ የሚፈጸመው ባለው አንገብጋቢነት እና የመልዕክት ክብደት እንጂ እንዴት በተናጋሪው የፆታ ልዩነት ሊሆን ይችላል? ለሚለው ጥያቄ አጥጋቢ ምላሽ አያስገኝም።

ከዚህ በላይ የቀረበው ትንታኔ እንደሚያመለክተው፣ ባህሉ በሴቶች ላይ ገደብ በመጣሉ ሳቢያ በሽምግልና ተቋሙ እንዳይሳተፉ እና ሚናቸውን እንዳይወጡ አድርጓል።

**የውጤት ማብራሪያ**

በዚህ ንኡስ ክፍል ከጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎቸ አንጻር፣ ከቀደምት ጥናቶች ውጤት እና ንድፈሐሳቦች ጋር እየተመሳከረ የጥናቱ ማብራሪያ ቀርቧል።

ከጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች አንዱ "በሰሜን ሸዋ ማህበረሰብ ዘንድ ለግጭት መንስኤ የሆኑትን ጉዳዮች መመርመር" የሚል ነው። የመረጃ ትንተናው ውጤት እንደሚያመለክተው፣ የስነምግባር ጉድለት፣ የሀብት ክፍፍል እና አስተዳደር በዋነኛነት ይጠቀሳሉ።

| **የግጭት መንስኤዎች** | **የግጭቱ ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| የእርሻ መሬት | ○ ድንበርተኞች<br>○ የቤተሰብ አባላት |
| የግጦሽ መሬት | ድንበርተኞች |
| ድንበር መግፋት | ድንበርተኞች |
| የሀብት ክፍፍል እና አስተዳደር | ○ ባል እና ሚስት<br>○ የቤተሰብ አባላት |
| ስንፈተ ወሲብ | ባል እና ሚስት |
| ውርስ | የቤተሰብ አባላት |
| የመስኖ ውሃ አጠቃቀም | ድንበርተኞች |
| ስካር | የመጠጥ ቤት ታዳሚዎች |

ሌላው ዝርዝር ዓላማ "በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ የሴቶች ተሳትፎን መለየት" የሚል ነበር። የመረጃ ትንታኔው ውጤት እንደሚጠቁመው፣ ለሽምግልና የሚመረጡት ወንዶች ናቸው።

ስለሆነም ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋሙም አባዊ ነው። በወንዶች የበላይነትና ጠቅላይነት የሚመራ ስለሆነ ይህ ተቋም ሴቶች የማይሳተፉበትን አሳማኝ ያልሆነ ምክንያት ያቀርባል። ሴቶች ለሽምግልና የሚበቃ አቅም እና ወኔ የላቸውም የሚል እምነት በህብረተሰቡ ስነልቦና ተፀንሶ እንዲጎለብት አድርጓል።

የእንስታውያኑ ንድፈሐሳብ እንደሚያስረዳው፣ ተባእትነትና እንስትነት ማህበራዊ ባህል እንጂ ተፈጥሮአዊ አይደለም። በጾታ ልዩነት ላይ የተመሰረተ ልማዳዊ የስራ ክፍፍል የሚያሳየውም ይህንኑ ነው። ሆኖም ግን ሴትነት ለፍርድ የማያበቃ ተፈጥሯዊ ምክንያት የለውም።

የበላይነትን የመቆጣጠር ስልት ሆን ተብሎ እንደሚተገበር የእንስታውያኑ ንድፈሐሳብ ይገልጻሉ። የግጭት አፈታት ሂደቱን ወንድ ሽማግሌዎች በበላይነት እንደመሩት እና እንደቋጩት ጥናቱ አመልክቷል። ይህም በአካባቢው የሀገር ሽማግላ ሆኖ የሚመረጠው ማህበራዊ ተሰሚነት፣ የመናገር ችሎታ፣ የኢኮኖሚ አቅም ያለው ወንድ ነው ከሚለው የ[14] ግኝት ጋር

ይደጋገፋል። ይህም በሴቶች ላይ ኢፍትሃዊነት እንዲጉለብት ምክንያት መሆን ችሏል።

ሦስተኛው ዝርዝር ዓላማ "ባህላዊ የግጭት መፍቻ ብልሃቶቹ ምን ምን ደካማ እና ጠንካራ ጎን እንዳላቸው ነቅሶ ማውጣት" ነው።

የትንታኔው ውጤት እንደሚያሳየው፣ በዞኑ የሚካሄደው የሽምግልና ስርዓት ጠንካራ ጎን የማህበረሰቡን ችግር ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ሳይባባስ በፍጥነት ለመፍታት ማስቻሉ ነው። ይህም ከ[14] ግኝት ጋር የተሰናኘ ነው።

በደካማ ጎንነት የተነሱት ደግሞ ሴቶች የማህበረሰቡ ግማሽ አካል ሆነው ሳለ በሽምግልና ምርጫ በአባልነት አለማካተቱ፣ የሴቶችን ማህበራዊ ኃላፊነት፣ አቅም እና ችሎታ ዝቅ አድርገው ከሚያቀርቡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች አለመታቀቡ፣ ለአባዊ ስርዓት ትኩረት በመስጠት በሴቶች ላይ ኢፍትሃዊነት ማስፈኑ ናቸው። ይህም የኡጋንዳ ሥነቃሎች የአባዊ ስርዓትን በማህበረሰቡ ዘንድ የሚተክሉ እና የሚጠናክሩ ናቸው ከሚለው የ[10] ግኝት ጋር ይስማማል።

## ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ፣ በሰሜን ሸዋ ዞን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎና ሚና ምን እንደሚመስል መርምሮ ማሳየት ነው። በጥናቱ እንደታየው በዞኑ የግጭት መንስኤዎች ናቸው ተብለው የተጠቀሱት የእርሻና የግጦሽ መሬት እጥረት፣ ስርቆት፣ ስንፈተ ወሲብ፣ ስካር፣ ውርስ፣ የሀብት ክፍፍል እና አስተዳደር ናቸው። በተደጋጋሚ ዋነኛ የግጭት መንስኤ ሆነው የተገኙት የእርሻ መሬት፣ የባልና የሚስት አለመግባባት፣ የሀብት ክፍፍል እና አስተዳደር ናቸው።

ባህላዊው የግጭት መፍቻ ዘዴ የተጋጩት ወገኖች በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች ፊት ቀርቦ የግጭቱን መንስኤ አስረድቶ መረጃ አቅርቦ፣ ምስክር ቆጥሮ ለመርታት የሚሄድበት መንገድ ነው። ይህ ስልት በአብዛኛው ወንድ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶች የሚመሩት የሽምግልና ስርአት ነው።

ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትና ዘዴዎች ከዘመናዊው የፍትህ ተቋማትና ስርአት ጋር በንጽጽር ሲታዩ ጊዜን፣ ጉልበትን እና የንዘብ ወጪን ይቀንሳሉ፤ ግጭቱ ሳይባባስ ቶሎ መፍትሄ ያስገኛሉ።

ነገር ግን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋሙ ሴቶችን አሳታፊ አላደረገም። በዚህ ሳቢያም የተዳፈኑ የትዳር ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ማግኘት እንዳልቻሉ ጥናቱ አረጋግጧል።

## ምክረሐሳብ

ለባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት፡- በባህላዊ የሽምግልና ስርዓት የሴቶች ተሳትፎና ሚና እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን ጥናቱ አመልክቷል። ስለሆነም በወንዶች የበላይነት እና ብቸኛ ውሳኔ ሰጭነት የተሟላ እና ፍትሀዊ መፍትሄ ለማግኘት ያስቸግራል። ስለሆነም በሽማግሌ መረጣ ሂደት ሴቶችን በአባልነት ማካተት እንዲችሉ ይህን ጉዳይ በሚመለከት ለአገር ሽማግሌዎች ሥልጠና ቢሰጣቸው።

ለፖሊሲ አውጪዎች፡- እውነታኛውን እና ትክክለኛውን የሴቶችን ባህላዊ፣ ጥበባዊ፣ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ የሚያጸባርቁ አዳዲስ ተረቶችን እና ቃል ግጥሞችን መጻፍ፣ ማሳተም፣ መተረክ እና ማሰራጨት የሚያስችል ፕሮጀክት ቢነደፍ እና በፖሊሲ ቢታቀፍ፣

ለትምህርት ባለሙያዎች፡- በይዘታቸው ስርዓተጾታ አድልዎ የሚታይባቸው ተረቶች እንደገና ተቃንተው (Reconstract) ቢጻፉ እና በመማሪያ መጻሕፍት ቢካተቱ፣

ለጥናት አድራጊዎች፡- ይህ ጥናት የተካሄደው በሰሜን ሸዋ ዞን ተወስኖ ስለሆነ ጥልቀት እና ስፋት ያለው ግብረመልስ ለማግኘት እንዲቻል በሌሎች የክልሉ ዞኖች በሚገኙ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶችም ቢጠኑ የሚሉ ናቸው።

## ማጣቀሻ ጽሑፎች


1. Fisher R: Social Psychology፡ An Applied Approach. New York: St.Martins, 1982.

2. Gold DL: Webster's Ninth New Collegiate Dictionary. 1983.

3. ደስታ ተክለወልድ። አዲስ ያማርኛ መዝገበቃላት። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም፣ 1963።

5. Menkel-Meadow C: The historical contingencies of conflict resolution. IJCER. 2013:1-32.

6. Butina MA: narrative approach to qualitative inquiry. Clinical laboratory science. 2015,1; 28(3):190-6.

7. Cresswell JW: Five qualitative approache to inquiry, in JW. Cresswell (2007) Qualitative inquiry and research method: Choosing among five approaches 2007.

8. Pierik B: Patriarchal power as a conceptual tool for geneder history. Rethinking History 2022, 26:1, 71-92.

9. Abasi K: “Gendering social Destiny in the proverbs of the Baganda: reflections on boys and girls becoming men and women”, Journal of African cultural studies 2005,17: 2.

10. ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል። የኢትዮጵያ ባህል ጥናት ቡልጋ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ፣ 1960።

11. Giday D: Traditional mechanism of conflict resolusion in Ethiopia. Addis Ababa, St. George printing press, 2000

12. Habtamu W: Conflict resolution in the families of nine ethnic groups in Ethiopia. The Ethiopian Journal of Education, 1998,18(2):19-40.

13. Yohannes B: Conflict and Conflict resolusion among the people of Chihera: Micro level case study from six Kebele in North Gonder.MA thesis, AAu, 1998.

14. MacDonald DA: Fieldwork: Collecting oral literature, 1972.

15. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። 1962። መጽሐፍ ቅደስ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም።

16. Gillo MD: Fundamentals of hermeneutics as a qualitative research theoretical framework. European Journal of Education and Pedagogy. 2021, 20, 2(3):42-5.

17. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማእከል። አማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣1993።